# ትምህርት 56

1. ምሳሌ ምንድን ነው?

ሀ- ምሳሌ የእግዚአብሔርን እውነት የሚያስተምር ታሪክ ነው።

2. ኢየሱስ ሰዎችን በምሳሌ ማስተማር የጀመረው ለምንድን ነው?

ሀ- ምንም እንኳን ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ቢከተሉም በኢየሱስ ስላላመኑ።

3. በምሳሌው ውስጥ ዘሩ ምንድን ነው?

ሀ- ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

4. በምሳሌ ውስጥ ዘሪው ማን ነው?

ሀ- ዘሪው የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምረው ሰው ነው።

5. በመንገድ የሚመሰሉት የትኞቹ ሰዎች ናቸው?

ሀ- ልባቸው ጠንካራ የሆኑ ሰዎች ናቸው።

ለ- እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል ወደ ልባቸው ዘልቆ መግባት አይችልም።

ሐ- ሰይጣን መጥቶ ቃሉን ይወስድባቸዋል።

6. በጭንጫ መሬት የተመሰሉት የትኞቹ ሰዎች ናቸው?

ሀ- እነዚህ ሰዎች ላይ ላዩን ብቻ «በእግዚአብሔር እናምናለን» የሚሉ ውስጣቸው ሲታይ ግን እምነት የሌላቸው ሰዎች ናቸው።

7. እሾኽ ባለበት መሬት የተመሰሉት የትኞቹ ሰዎች ናቸው?

ሀ- እነዚህ ሰዎች «በእግዚአብሔር እናምናለን» የሚሉ ነገር ግን የፍላጐታቸው መሟላት ከእግዚአብሔር የበለጠ አስፈላጊያቸው የሆኑ ሰዎች ናቸው።

8. በመልካሙ መሬት የተመሰሉት የትኞቹ ሰዎች ናቸው?

ሀ- እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው ሙሉ በሙሉ ያመኑና ብዙ ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው።

- ኢየሱስ እስኪመሽ ድረስ ሕዝቡን ማስተማሩን ቀጠለ።

- ከዚያም ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ የገሊላን ባሕር ለማቋረጥ ወደ ጀልባ ውስጥ ገቡ።

ማርቆስ 4፡35-37

35- ያን ቀን በመሸ ጊዜ፣ «ወደ ማዶ እንሻገር» አላቸው።

36- እነርሱ ሕዝቡን ትተው በጀልባዋ ውስጥ እንዳለ በዚያው ይዘውት ሄዱ፤ ሌሎች ጀልባዎችም አብረውት ነበሩ።

37- በዚህ ጊዜ ኀይለኛ ዐውሎ ነፋስ ተነሣ፤ ማዕበሉም ውሃ እስኪሞላት ድረስ ጀልባዋን ያናውጣት ነበር።

- ባሕሩን በማቋረጥ ላይ ሳሉ ምን ሆነ?

- ኃይለኛ ዐውሎ ነፋስ ተነሣ።

- ዐውሎ ነፋሱ በኃይል ይነፍስ ስለ ነበር ማዕበሉ ጀልባዋ ለመስጠም እስክትቃረብ ድረስ ያናውጣት ነበር።

- ኢየሱስ የት ነበር?

ማርቆስ 4፡38ሀ

38- ኢየሱስ ግን ትራስ ተንተርሶ ከጀልባዋ በስተ ኋላ በኩል ተኝቶ ነበር።

- ኢየሱስ የተኛው ለምን ነበር?
- ኢየሱስ ቀኑን ሙሉ ሕዝቡን ሲያስተምር ስለነበር ደክሞት ስለ ነበር።

- ኢየሱስ ለምን ደከመ?
- ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ አምላክ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ሰው ስለ ነበር።

- ጀልባዋ ልትሰጥም ስለ ነበር ደቀ መዛሙርቱ ምን አደረጉ?

ማርቆስ 4፡38ለ

38- እነርሱም ቀስቅሰውት፣ «መምህር ሆይ፤ ስናልቅ አይገድህምን?» አሉት

- ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን ቀሰቀሱት
- ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን ምን አሉት?
- «ስንሰምጥ አይገድህምን?»

- ኢየሱስ አልገደደውም ነበር?
- ኢየሱስ በጣም ይገድደው ነበር።

- ኢየሱስ ምን አደረገ?

ማርቆስ 4፡39

39- እርሱም ተነሥቶ ነፋሱን ገሠጸው፤ ባሕሩንም፣ «ጸጥ፣ ረጭ በል!» አለው ነፋሱም ጸጥ፣ ረጭ አለ፤ ፍጹምም ጸጥታ ሆነ።

- ኢየሱስ ምን አደረገ?

- ኢየሱስ ነፋሱንና ባሕሩን ጸጥ እንዲል አዘዘ?

- ከዚያስ ምን ሆነ?

- ነፋሱ ዝም አለ ባሕሩም ሙሉ በሙሉ ረጭ አለ።

- ኢየሱስ ነፋሱንና ባሕሩን ጸጥ እንዲሉ ማዘዝ የቻለው እንዴት ነው?

- ምክንያቱም ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ ነው።

- በመጀመሪያ ነፋሱን ማን ፈጠረው?

- ኢየሱስ።

- በመጀመሪያ ባሕሩን ማን ፈጠረው?

- ኢየሱስ።

- ነፋሱና ባሕሩ ለኢየሱስ የታዘዙት ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ነፋሱንና ባሕሩን የፈጠረው ኢየሱስ ስለሆነ ነው።

- ነፋሱና ባሕሩ ጸጥ ካለ በኋላ ኢየሱስ ምን አለ?

ማርቆስ 4፥40

40- ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን፣ «ስለ ምን እንዲህ ፈራችሁ? እስከዚህ እምነት የላችሁምን?» አላቸው።

- ኢየሱስ እምነት ለምን እንዳጡ ጠየቃቸው።

- ኢየሱስ ምን ማለቱ ነበር?

- ኢየሱስ እርሱ አምላክ መሆኑን ለምን እንዳላመኑ እየጠየቃቸው ነበር።

- ከዚያስ ደቀ መዛሙርቱ ምን አሉ?

ማርቆስ 4፥41

41- እነርሱም በፍርሃት ተውጠው እርስ በርሳቸው፣ «ነፋሱም ሞገዱም የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው?» ተባባሉ።

- ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ሰዎችን ሲፈውስ ቢያዩም ነፋስን አዝዞ ጸጥ እንዲል ሲያደርግ አይተው አያውቁም ነበር።

- ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ አጋንንትን ከሰዎች አዝዞ ሲያስወጣ ቢያዩም ማዕበልንና ባሕርን አዝዞ ጸጥ እንዲል ሲያደርግ አይተው አያውቁም ነበር።

-ኢየሱስ የማይችለው አንድም ነገር የለም።

- ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው።

- ቀጥሎም ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ በባሕሩ ወደሌላኛው ዳርቻ ሄዱ።

ማርቆስ 5፥1-4

1- ባሕሩን ተሻግረው ጌርሴኖን ወደ ተባለ አገር መጡ።

2- ኢየሱስ ከጀልባ እንደ ወረደ፣ ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው ከመቃብር ቦታ ወጥቶ ሊገናኘው ወደ እርሱ መጣ።

3- ይህ ሰው በመቃብር ቦታ ውስጥ የሚኖርና ማንም በሰንሰለት እንኳ ሊያስረው የማይችል ነበር።

4- ብዙ ጊዜ በእግር ብረትና በሰንሰለት ይታሠር ነበር፤ ነገር ግን የእጅ ሰንሰለቱን ይበጥስ፣ የእግር ብረቱንም ይሰብር ነበር። ማንም ይዞ ሊያቈየው የሚችል አልነበረም።

- በአጋንንት የተያዘው ሰው በቁጥጥራቸው ሥር ካዋሉት ከአጋንንቱ ሁሉ ኃይል ራሱን ማዳን ችሎ ነበር?

- አልቻለም።

- ሌሎች ሰዎችስ ይህን ሰው በቁጥጥራቸው ሥር ካዋሉት ከአጋንንት ኃይል ሊያድኑት ችለዋል?

- አልቻሉም።

- ሰዎች ሰውየውን በማሠር ሊረዱት ሞክረው ነበር።

- ነገር ግን በውስጡ የነበሩት አጋንንት ኃይለኞች ስለ ነበሩ ሰዎች ያሠሩትን የብረት ሰንሰለት በጣጠሱት።

ማርቆስ 5፡5

5- በመቃብሮቹና በተራራዎቹ መካከል ቀንና ሌሊት እየተዘዋወረ በመጮኽ ሰውነቱን በድንጋይ ይቈራርጥ ነበር።

- አጋንንት ሰዎችን እንደሚጠሉ በምን እናውቃለን?

- አጋንንት ይህን ሰው ሰዎች በሚቀበሩበት ዋሻ ውስጥ እንዲኖር በማስገደዳቸው።

- አጋንንት ይህን ሰው የራሱን አካል እንዲቆራርጥ በማድረጋቸው።

- አጋንንት ሰውየውን ባሪያቸው አደረጉት።
- አጋንንት ሰውየው ራሱን እንዲገድል ፈለጉ።

- ይህ ሰው ብዙ አጋንንት ስላለበት እጅግ በጣም ጐድተውት ነበር።

- ሰዎች ሁሉ የአጋንንት ባሪያዎች ሆነው ስለተወለዱ፥እኛ ሁላችንም እንዲዚህ ሰው የአጋንንት ባሪያዎች ነን።

- የአጋንንት ሁሉ አለቃ ማን ነው?
- ሰይጣን።

- ሰይጣንና አጋንንቱ እኛ ሁላችንንም ይጠላሉ።
- ሰይጣንና አጋንንቱ የሚፈልጉት ሰዎችን ማጥፋት ብቻ ነው።

- ሰይጣንና አጋንንቱ እኛን የሚረዱ ቢመስሉም ይህን የሚያደርጉት እኛን ለማጥፋት ስለሚፈልጉ ብቻ ነው።

- ሕይወትህን የተቆጣጠሩት አጋንንት የሚረዱህ ሊመስሉ ይችላሉ።
- ነገር ግን ይህን የሚያደረጉት ሊያጠፉህ ስለሚፈልጉ ብቻ ነው።

- ሰይጣንና አጋንንቱ የሕይወት ዓላማቸው አንድ ብቻ ነው።

- ይኸውም የቻሉትን ያህል ሰዎችን ማጥፋት ነው።

- ሰይጣንና አጋንንቱ እግዚአብሔርን እንድታውቁና ከእነርሱ ኃይል ነጻ እንድትወጡ አይፈልጉም።

- ይህ ሰው ኢየሱስን ባየው ጊዜ ምን ተፈጸመ?

ማርቆስ 5፡6-7

6- ይህም ሰው ኢየሱስን ከሩቅ ባየው ጊዜ፣ ወደ እርሱ ሮጦ ከፊቱ ተንበርክኮ ሰገደለት፤

7- በታላቅ ድምፅ ጮኾም፣ «አንተ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ፤ ከእኔ ምን አለህ? እንዳታሠቃየኝ በእግዚአብሔር ይገዤሃለሁ!» አለው።

- አጋንንቱ ኢየሱስ አዳኝ አምላክ መሆኑን አውቀዋል?
- አዎን።

- አጋንንቱ የፈሩት ምን ነበር?

- አጋንንቱ የፈሩት ኢየሱስ ወደ እሳት ባሕር እንዳይሰድዳቸው ነበር።

- ከሰይጣን፥ ከአጋንንቱም የሚበልጠው ማን ነው?
- ኢየሱስ፤ እርሱም እግዚአብሔር።

- እግዚአብሔር ሰይጣንንና አጋንንቱን በፈለገው ጊዜ ወደ ዘላለማዊው የእሳት ባሕር ይሰዳቸዋል።

- ኢየሱስ አጋንንቱን ምን አላቸው?

ማርቆስ 5፡8-10

8- ይህንንም ያለው ኢየሱስ፣ «አንተ ርኩስ መንፈስ ከዚህ ሰው ውጣ!» ብሎት ስለ ነበር ነው።

9- ከዚያም ኢየሱስ፣ «ስምህ ማን ነው» ብሎ ጠየቀው። «ብዙ ነንና ስሜ ሌጌዎን ነው» አለው።

10- ከአገር እንዳያስወጣቸው አጥብቆ ለመነው።

- አጋንንት ኢየሱስን ማሸነፍ እንደማይችሉ ያውቃሉ?
- አዎን።

- ኢየሱስ በሰይጣንና በአጋንንቱ ላይ ሙሉ ሥልጣን አለው።

- በመጨረሻም ኢየሱስም ሰይጣንንና አጋንንቱን ወደ ዘላለማዊው የእሳት ባሕር ውስጥ ይሰድዳቸዋል።

- እግዚአብሔር ወደ ዘለዓለማዊው የእሳት ባሕር የሚጣሉትን ርኩሳን መናፍስት ለምን እናገለግላለን?

- ርኩሳን መናፍስትን ከማገልገል እግዚአብሔርን ማገልገል የተሻለ ነው።
- ከዚያስ ኢየሱስ ምን አደረገ?

ማርቆስ 5፡11-14

11- በአቅራቢያውም በሚገኝ ኮረብታ ላይ ትልቅ የዐሣማ መንጋ ተሰማርቶ ነበር።

12- ርኩሳን መናፍስቱም ኢየሱስን፣ «ወደ ዐሣማዎቹ ስደደን፤ እንድንገባባቸውም ፍቀድልን» ብለው ለመኑት።

13- እርሱም ፈቀደላቸው። ርኩሳን መናፍስቱም ወጥተው በዐሣማዎቹ ገቡባቸው፤ ሁለት ሺህ ያህል ዐሣማዎችም በገደሉ አፋፍ በመንደርደር ቍልቍል ወርደው በባሕር ውስጥ ሰጠሙ።

14- እረኞቹ ሸሽተው ሄዱ፤ ወሬውን በከተማና በገጠር አዳረሱት፣ ሕዝቡም የሆነውን ለማየት ካለበት ወጣ።

- አጋንንት ኢየሱስን ስለ ለመኑት ወደ ዓሣማዎቹ እንዲገቡ ፈቀደላቸው።
- ዓሣማዎች በሙሉ ሲሞቱ አጋንንቱም ሞተዋል?

- አልሞቱም።

- ዓሣማዎች በሙሉ ሲሞቱ አጋንንቱ ያልሞቱት ለምን ነበር?

- ምክንያቱም አጋንንት መናፍስት ስለሆኑ ነው።

- ምክንያቱም አጋንንት እንደ ሰዎችና እንደ እንስሳት አካል ስለሌላቸው ነው።

- ኢየሱስ አጋንንትን ወደ ዘላለማዊው የእሳት ባሕር ያልሰደዳቸው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር አጋንንትን የሚቀጣበት ጊዜ ስላልሆነ ነው።

-ይሁን እንጂ በመጨረሻ ኢየሱስ ሰይጣንንና አጋንንቱን ሁሉ ወደ ዘላለማዊው የእሳት ባሕር ይሰድዳቸዋል።

- በዚያ አካባቢ የሚኖሩት ሰዎች እዚያ መጥተው ምን አዩ?

ማርቆስ 5፡15

15- ወደ ኢየሱስም በመጡ ጊዜ፣ የአጋንንት ሰራዊት አድረውበት የነበረው ሰው፣ ልብስ ለብሶና አእምሮው ተመልሶለት በዚያ ተቀምጦ አዩት፣ ፈሩም።

- በአጋንንት ተይዞ የነበረው ሰው አሁንም የአጋንንት ባሪያ ነውን?
- አይደለም።

- ሰውየውን ከአጋንንት እስራት ነፃ ያወጣው ማን ነው?

- ኢየሱስ።

- ሰውየው ከእንግዲህ የአጋንንት ባርያ አይደለም።

- ሰውየው በአዳኙ አምላክ በኢየሱስ ነጻ ወጥቶአል።

- በዚያ አካባቢ የሚኖሩት ሰዎች ምን አደረጉ?

ማርቆስ 5፡16-17

16- ይህን ያዩ ሰዎችም አጋንንት ስላደረበት ሰው የተደረገውንና ስለ ዐሣማዎቹም ለሕዝቡ አወሩ።

17- ከዚያም ሕዝቡ አገራቸውን ለቆ እንዲሄድላቸው ኢየሱስን ይለምኑት ጀመር።

- ሰዎቹ ኢየሱስ አገራቸውን ለቅቆ እንዲሄድ የለመኑት ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ሰዎቹ ሞኞች ስለነበሩ ነው።

- ምክንያቱም ሰዎቹ ከእግዚአብሔር ይልቅ ስለ ዓሣማዎቻቸው ያስቡ ስለነበር ነው።

- አዳኙ አምላክ ኢየሱስእነርሱን ከሰይጣን ባርነት ነጻ ሊያወጣ መጣ፤ እነርሱ ግን ስለ ዓሣማዎቻቸው ብቻ ያስቡ ነበር።

- ዛሬ ብዙ ሰዎች እንደ እነርሱ ናቸው።

- ሰዎቹ ከኢየሱስ ይልቅ ስለ ዓሣማዎቻቸው ብዙ ያስባሉ።

- ሰዎች ከኢየሱስ ይልቅ ስለ ንብረታቸው ብዙ ያስባሉ።

- ነገር ግን ዓሣማዎቻችሁ ወይም ንብረቶቻችሁ ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ነፃ ሊያወጧችሁ ይችላሉ?

- አይችሉም።

- ከአጋንንት ነፃ የወጣው ሰው ኢየሱስን ምን አለው?

ማርቆስ 5፡18-20

18- ኢየሱስ ወደ ጀልባዪቱ በሚገባበት ጊዜ፣ አጋንንት አድሮበት የነበረው ሰው አብሮት ለመሄድ ለመነው።

19- ኢየሱስ አልፈቀደለትም፤ ነገር ግን፣ «ወደ ቤትህ ሂድ፣ ለዘመዶችህም ጌታ ምን ያህል ታላቅ ነገር እንዳደረገልህና ያሳየህን ምሕረት ንገራቸው» አለው።

20- ሰውየውም ሄደ፤ ኢየሱስ ያደረገለትን ነገር ሁሉ አሥር ከተማ በተባለው አገር ያወራ ጀመር፤ የሰሙትም ሁሉ ተደነቁ።

- ኢየሱስ ሰውየው ከእርሱ ጋር እንዲሄድ ያልፈቀደለት ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ኢየሱስ ሰውየው ለቤተሰቡና ለሌሎች ሰዎች እግዚአብሔር ያደረገለትን እንዲነግራቸው ስለፈለገ ነው።

- እግዚአብሔር ከሰይጣንና ከአጋንንቱ ኃይል ነፃ ካወጣን በኋላ እነርሱንም እንደዚሁ ነጻ ሊያወጣቸው እንደሚፈልግ ለሌሎች ሰዎች መንገር አስፈላጊ ነው።